# ዜና

□ትም 1 ???? ???? ????
?? ? ???



በዚህ እትም

አምዶች ገጽ

1-ርዕሰ አንቀፅ ---------------------------------------------2

2 -የሴክተሩ አጫጭር ዜናዎችና
አበይት ክንውኖች------------------------------------ 3

በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መንግሥት አቅም ግንባታ ሴክተር በመንግሥት ኪሚኒኬሽን
የሥራ ሂደት በ□□ሩ የሚዘጋጅ

# ርዕሰ አንቀጽ

## ውጤት ተኮር ምስረታችንን
## በባለንስድ ስከርካርድ ቅኝት መቅረጽ ጠቃሚ ነው!!!

በሀገራችን በመካሄድ ላይ ያለውን አዲስ የአሠራር ለውጥ ሂደት በመደገፍ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ስኬታማ ውጤት ማስመዝገብ ይቻል ዘንድ ውጤት ተኮር ስርዓት ምስረታችንን በባላንስድ ስኮርካርድ ቅኝት መቅረፅ ጠቃሚ ነው፡፡ ባለንስድስካር ካርድ በአፈፃፀም መለኪያነቱ ተቋማት ሊያሳኩ ካቀዷቸው ›ኢላማዎች በመነሳት አፈፃፀምን ከስትራቴጂያዊ ዕቅድ ጋር የሚያስተሳስር የዕይታ መስኮችን ለይቶ በማውጣት ስትራቴጅያዊ ግቦችን ለመለካት የሚያስችል ከመሆኑም ባሻገር የተቋማትን ስኬት ከተለያዩ ዕይታዎች አንፃር በመቃኘት ለደንበኞች /ተገልጋዮች/ እርካታ መፍጠር የሚያስችል፣ ተቋማት ውስጣዊ አቅማቸውን እንዴት አድርገው ማጠናከር እንደሚችሉ ግልፅ አድርጐ የሚያሳይ ሳይንሳዊ የአፈፃፀም መለኪያ መሳሪያ ሲሆን አገልግሎት ሰጪዎች መስራት ያለባቸውንና የሌለባቸውን ለመለየት ያስችላል፡፡ ቀደም ሲል በሀገራችን የውጤት ተኮር ምዘና ስርዓት የነበረ ቢሆንም ተግባርን እንጂ ውጤትን የማይመዝን፣ ከስትራቴጅያዊ ዕቅድ ጋር ያልተሳሰረ ከመሆኑም በላ□ ዕቅዱ ወደታች ተሸንሽኖ የሚወርድበት ዘዴ አመላካች ባለመሆኑ እንዲሁም የአመለካከት፣ የቴክኒክና የክህሎት ችግሮች ያሉበት በመሆኑ ከጅምር ያለፈ ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም፡፡በዚህ ምክንያት በመንግስትና በግል ተቋማት ተሞክሮ ውጤት የታየበት የውጤት ተኮር ስርዓት ማለትም ባላንስ□ ስኮር ካርድ ለሀገራችን ተስማሚና ተመራጭ ሆኗል፡፡ ውጤት ተኮር ስርዓት ከነባሩ የሚለየው ከግቦች ጋር በመተሳሰሩ፣ የመለኪያውን አይነት፣ የአፈፃፀም መረጃ የሚሰበስብበት ወቅት፣ የመረጃውን ጥራት በግልፅ ከማሳየቱም በላይ ከአድልዎ አሰራር ነፃ መሆኑ ሚዛናዊና ትክክለኛውን ነገር በመለካት ተገቢነቱን በማረጋገጡ ነው፡፡ በመሆኑም ተቋማት ውጤት ተኮር አፈፃፀም ማስመዝገብ እንዲችሉ ያረጀውንና ኋላ ቀር አፈፃፀም አመራር ዕሳቤዎች ላይ ተመስርቶ የቆየውን አሠራራቸውን በውጤት ተኮር ስርዓት መቀየር ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ የተጀመረውን የተቋማዊ ሽግግር ሥራ ምሉዕ በማድረግ በሀገራችን በመካሄድ ላይ ያለውን ልማት ለማፋጠን፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባትና መልካም አስተዳደር ለማስፈን ይቻል ዘንድ ከአመራር ጀምሮ እስከታችኛው አካል ድረስ ለተግባራዊነቱ መረባረብ አለብን፡፡

*በሠናይት አበበ*


**ዕትም 1**

□ህሳስ 2002 □ም

አቅም ግንባ□ ቢሮ

በመንግሥት ኮሚኒኬሽን

የሥራ ሂደት በየወሩ

የሚዘጋጅ



**ዋና አዘጋጅ**

ሚልኪያስ እስራኤል

**አዘጋጆች**

ሰናይት አበበ

ሰብለ አበበ

*ካሜራና ቪዲዮግራፈር*

*ደነቀው ከበደ*

*የኮምፒውተር ጽሁፍና ዲዛይን ሥራ*




*አስናቀች መዝገቡ*

# የክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ አመታዊ ጉባኤ አካሄደ

የክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ ሐምሌ 29/2001 ዓ.ም በሥራ አመራር የስልጠና አዳራሽ አመታዊ ጉባዔውን አካሄደ፡፡ ጉባኤው ለሁለት ተከታታይ ቀናት የቆየ ሲሆን በአቅም ግንባታ ቢሮ ያሉ የስራ ሂደት ባለቤቶች፣ የ13 ዞኖችና የ8 ልዩ ወረዳዎች አቅም ግንባታ ሀላፊዎች የጉባዔው ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

በዕለቱ የ2001 ዓ/ም የአቅም ግንባታ ቢሮዎች ስራ አፈፃፀም የተገመገመ ሲሆን በቢሮው የሚከናወኑ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም፣ የወረዳ መልካም አስተዳደር፣ የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ እና በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ዘርፎች የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ የክልሉን የአፈፃፀም ሪፖርት አቶ ጣሰው ገብሬ የአቅም ግንባታ ቢሮ ኃላፊ አቅርበዋል፡፡ በጉባኤው በሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የተከናወኑ ተግባራት ሪፖርት ቀርቦ ውይይት ከተደረገ በኋላ ጠንካራ ስራዎች እንዲቀጥሉ እንዲሁም በቀጣይ መከናወን ያለባቸው ጉዳዮች ላይ ሠፊ ውይይትተካሂዷል፡፡

በመጨረሻም በክልሉ በሁለተኛ ዙር ተጠንተው ወደ ሙሉ ትግበራ የገቡ ሴክተሮች እየተደረገ ያለው ድጋፍ እንዲቀጥል፣ ምርጥ ተሞክሮዎች የማስፋት ተግባር በሠፊው መቀጠል እንዳለበት አሳስበው በ2002 የስራ ዘመን በሚከናወኑ እቅዶች ላይ ውይይት ከተደረገ በኋላ እቅዱን ለማስፈፀም የግብ ስምምነት ተፈራርመው ጉባኤው ተጠናቋል፡፡

**የተሳኩ ተሞክሮዎችን በማስፋት የኢትዮጵያን ህዳሴ እናረጋግጣለን !**

# የኢኮቴ የስራ ሂደት በክልሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እያስፋፋ ነው

በአቅም ግንባታ ቢሮ የኢኮቴ /የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ/ ዋና የስራ ሂደት በክልሉ ውስጥ ያሉ ቢሮዎች፣ ዞኖችን ወረዳዎች የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ አቅም የመፍጠር ሥራ እየሠራ መሆኑን በአቅም ግንባታ ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የኢኮቴ ዋና የሥራ ሂደት ባለቤት አቶ ዓይናለም ፀጋዬ ገለፁ፡፡

እንደ ኃላፊው ገለፃ የክልሉ ፀረ-ሙስና ቢሮ፣ ግብርና ቢሮ፣ አርብቶ አደር፣ ብዙሀን መገናኛ፣ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን፣ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ ርክሰ መስተ□□ር፣ □ጣቶች ጉዳይ ቢሮ፣ □ልል □ሊስ ኮሚሽን web-page ተከፍቶላቸው የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ ሲሆኑ በቀጣይም ለ21 ቢሮዎች በመሰራት ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ለ13 ዞኖች፣ ለ3 ወረዳዎችና ለ8 ልዩ ወረዳዎች ድረ-ገፅ (website) በመስራት ላይ እንደሚገኝ አስ□□ቀ□ለ□፡፡ የኔትወርክ ዝርጋታ□ ከዚህ በፊት በሁሉም ቢሮዎች ያልነበረ ሲሆን በየስራ ሂደቱ ላሉ ባለሙያዎች በግል ያስፈልግ የነበረውን ፕሪንተር በኔትወርክ በማገናኘት በአንድ የሥራ ሂደት አንድ ፕሪንተር ብቻ እንዲጠቀሙ በማድረግ ወጪ መቆጠብ መቻሉን ገልፀዋል፡፡ በክልሉ የሚገኙ ቢሮዎች መረጃዎችን በመለዋወጥ አገልግሎት አሠጣጡ ቀልጣፋ እንዲሆን ከማስቻሉም ባሻገር የመስሪያ ቤቶችን መረጃ ለሚፈልጉ ተጠቃሚዎች በቀላሉ ማግኘት የሚያስችል መሆኑን ጠቁመዋል፡፡



የኢኮቴ የሥራ ሂደት ባለሙያዎች በሥራ ላይ

በተጨማሪም በፀረ-ሙስና ቢሮ የተከናወነው የሶፍትዌር ዝርጋታ በክልሉ ውስጥ የሚፈፀሙ ሙስናዎችንና ብልሹ አሠራሮችን ማንኛውም ሰው ለመ/ቤቱ ጥቆማ ማድረግ እንዲቻል በዘመናዊ መልክ እንዲሠሩ ያስቻላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

እንደ ስራ ሂደቱ ባለቤት ገለፃ በታክስ አስተዳደር ቢሮ የተከናወነው የኔትወርክ ዝርጋታ ተገልጋዮች ወደ ክልል ቢሮ ታክስ ለመክፈል በመምጣት ይደርስባቸው የነበረው ለአላስፈላጊ ወጪና ጊዜ ብክነት በመከላከል እዚያው ባሉበት ሆነው ክፍያ በማከናወናቸው ወጪና ጊዜ ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ተችሏል ። ከዚህም በላይ የስራ ሂደቱ የጥገና ባለሙያዎች በክል ከባድ ጥገና የሚፈልጉትን ጥገናዎች በስራ ሂደቱ የጥገና ክፍል በማምጣት የሚጠግኑ ሲሆን በአንዳንድ ቦታዎችም በአካል በመገኘት የጥገና ስራ እንደሚያከናውኑ ታውቋል።



የኢኮቴ የሥራ ሂደት የጥገና ባለሙያዎች በሥራ ላይ

ይህ በጥገና ባለሙያዎች የሚከናወነው ተግባር በገንዘብ ሲሰላ በዓመት ለጥገና ይወጣ የነበረውን ከ2.6 ሚሊየን ብር በላይ መቀነስ እንዳስቻለ ታውቋል። በኢኮቴ የስራ ሂደት በተደረገው ጥረት ከክልሉ የተውጣጡ 6000 መምህራን በሁለት ዙር የቪዲዮ ኮንፍረንስ ስልጠና በመስጠት 3.1 ሚሊዩን ብር በላይ ለአበል ፣ ለትራንስፖርትና ለተለያዩ ጉዳዮች ይወጣ የነበረውን ወጪ ማትረፍ ከመቻሉም በላይ ሠልጣኞቹ መረጃዎችን ሳይሸራርፉ ከምንጩ ማግኙት እንዲችሉ ያስቻለ መሆኑ ተገልጿል።

**ከታላላቅ ሰዎች አንደበት**

- እውነተኛ መሪ ማለት እሱ ባይኖርም አለ ተብሎ የሚታመንት ነው ። /ሆሜር/
- የማንነት መገለጫ ድርጊት እንጂ የቃላት ቅጥፈት አይደለም!!

## በስራ አመራር ተቋም የስልጠና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጠ።

በሥራ አመራር ኢንስቲትዩት የስልጠና ባለሙያዎች በአቅም ግንባታ ሴክተር በዋና የስራሂደቶች ላ□ ላሉ ፈፃሚዎች ከ02/12-12/12/01 ድረስ ለአስር ተከታታይ ቀናት የቆየ የአሰልጣኞች ስልጠና /TOT/ ስልጠና በሥራ አመራር አዳራሽ ተሰጥቷል። ስልጠናው በዋናነት ዓላማ ያደረገው በክልላችን በአቅም ግንባታ ሴክተር ከዋና የስራ ሂደት የተውጣጡ ባለሙያዎችን ከሙያቸው የተያያዘ ክህሎትን በማዳበር በክልሉ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግስት ሠራተኞች ስልጠና በሚሰጡበት ጊዜ እንደ አሰልጣኝ ሊኖራቸው የሚገባውን አጠቃላይ ክህሎት ጨብጠው በሥራ ላይ እንዲያዉሉ ለማስቻል መሆኑ ታውቋል። ስልጠናው ያተኮረው አጠቃላይ በስልጠና ምንነት፣ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት፣ የስልጠና ሰነድ አዘገጃጀት፣ የአመቻችነት እና የንግግር ክህሎት እንዲሁም የስልጠና ግምገማ ሂደት ላይ ሲሆን አሳ□□ በሆነ መንገድና በተሟላ የስልጠና ማቴሪ□ል የተሰጠ በመሆኑ ጥሩ ግንዛቤ □ስጨበጠ መሆኑን አንዳንድ ሰልጣኞች ከሰጡት አስተያየት ለመረዳት ተችሏል። አቶ □□ አንበርብር የስራ አመራርና የመሪነት ልማት ዋና የስራ ሂደት ባለቤት እና የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር በስልጠናው መብቂያ ባሰሙት ንግግር ስልጠናውን በንቃት በመሳተፍ ለወደፊቱ በ□□ረ□ው ለሚሰጡ ስልጠናዎች ዓሩ እውቀት ጨብጣችሁ ለዚች ቀን በመብቃታችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ ካሉ በኋላ ለተሳታፊዎች የተዘጋጀውን የምስክር ወረቀት በመስጠት ስልጠናው ተጠናቋል።

# በፕሮጀክት ስራ አመራር ክትትልና ግምገማ ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ ::

በአቅም ግንባ□ ቢሮ □ለ□ዓ ፕሮግራሞችና ፓኬጆች □ና □ሥራ ሂደት የተዘጋጀው ስልጠና በዋና □ሥራ ሂደቶች እና በልማት □ቅ□ ፣ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ □□□ የስራ ሂደት ለሚሰሩ ባለሙያዎች በፕሮጀክት ስራ አመራር ክትትልና □ም□ማ □ሪ□ ከ02/01/02-06/001/02 □ም ለአምስት ተከ□□□ ቀናት የቆየ ስልጠና በስራ አመራር አዳራሽ ተሰጥቷል ::



የስልጠናው መክፈቻ ሥነ-ስርዓት

ስልጠናውን የሰጡት የ□ሮ□ራም ክትትልና ግምገማ አማካሪ የሆኑት አጋንዳዊው በጉ ፈቃደኛ ሚ/ር ባሴንቫ ጁሌየስ ሲሆኑ ስልጠናው በሁለት ዙር የሚጠናቀቅ እንደሆነም □□ቋል::

የስልጠናው ዓላማ ሰራተኞች በስራቸው ላይ እያሉ የውስጥ አቅም በመገንባት የተሻለ ስራ ለመስራት የሚያስችል አቅም ለመፍጠር ታስቦ እንደሆነ ተገልፆዋል::



በፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ላይ የተሰጠ ስልጠና

አቶ አያኖ ሱመኖ የአቅም ግንባ□ ቢሮ ምክትል ሃላፊና የለውጥ ፕሮግራሞችና ፓኬጆች ዋና የስራ ሂደት ባለቤት በስልጠናው ማብቂያ ባሰሙት ንግግር ይህንን ስልጠና ለክልሉ ለሁሉም ሴ□ተር መሥሪያ ቤቶች ለመስጠት □□ሰበ ቢሆንም በአቅም ውስንነት □ተነሳ የሴ□ተሩን ባለሙያዎች አቅም ለመገንባት ከሁሉም የስራ ሂደቶች ባለሙያዎች ተውጣጥተው ስልጠናው እንዲሰጥ ተደርጓል ሲሉ □ል□□ል፡፡

አያይዘውም የስልጠናው ዓላማ ውስጣዊ አቅም ግንባታ ሲሆን □□ሮጀክት ስራዎች እንደልምድ አዋላጅ ከሳይንስ □·□ □ሚሰራ በመሆኑ ይህንን ችግር በተወሰነ □ረ□ ለመቅረ□ ለየት ባለ መልኩ ከተግባር □ር ተ□□ዞ □ተሰ□ ስልጠና በመሆኑ የሠራተኛውን አቅም የገነባ ነው ሲሉ ገልፀዋል ፡፡

አንዳንድ የስልጠና ተሳታፊዎችን አነጋግረን በሰጡት አስተያየት ስልጠናው በቀጥ□ ከስራችን ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ አቅማችንን አጎልብተን መስራት ያስችለን ዘንድ ለወደፊቱ ሰፋ ባለ ሁኔታ መሰጠት እንዳለበት □ቁመ□ል፡፡ አቶ አያኖ በስልጠናው መዝጊያ ሰራተኛው ይህንን ስልጠና መነሻ በማድግ ከወቅቱ ጋር

የተገናዘበ አሰራር ለመከተል የራስን አቅም መገንባቱ ወሳኝ በመሆኑ በግል ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል ሲሉ መልካም የሥራ ዘመን በመመኘት የስልጠናውን ማብቃት አብስረው ለተሳታፊዎች የተዘጋጀውን የምስክር ወረቀት በመስጠት ስልጠናው ተጠናቋል፡፡



የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስነ ስርዓት



# የሰንደቅ ዓላማ ቀን በደማቅ ሥነ-ሥርዓት ተከበረ

ብሄራዊ የሠንደቅ ዓላማ ቀን በሀገር አቀፍ ደረጃ አዲሱ ዓመት በገባ በሁለተኛ ሳምንት እንድከበር መወሰኑን መነሻ በማድረግ ዘንድሮ በዓሉ መስከረም 25 ቀን 2002 ዓ.ም በአቅም ግንባታ ቢሮ በደማቅ ስነስርዓት ተከብሯል፡፡

በዕለቱ ለበአሉ አከባበር የተዘጋጀ የኢትዮጵያ ህዝብ ብሄራዊ መዝሙር የያዘ ጽሁፍና የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ ለበዓሉ ተሳታፊዎች ተሰራጭቷል፡፡



የባንዲራ ስነስርዓት አከባበር

አቶ ጣሰው ገብሬ የደቡብ ክልል አቅም ግንባታ ቢሮ ሀላፊ በበዓሉ አከባበር ስነስርዓት ላይ ባሰሙት ንግግር ሠንደቅ ዓላማችን የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የተለያዩ እምነቶችን ይዘው በእኩልነትና በመከባበር የሚኖሩበት ዘመን ላይ የደረስንበት ድህነትንና ኋላቀርነትን ድል ለማድረግ ቃል የምንገባበት፣ የሰንደቅ ዓላማችንን ፍቅርና ክብር በልማት የምንገልፅበት ዕለት መሆኑን ገልፀ□ የኢትዮጵያ ህዝብ ሰንደቅ ዓላማ መዝሙር እየተዘመረ ሰንደቅ ዓላማችንን በክብር አውጥተዋል፡፡ በመጨረሻም ለ2002 ዓ/ም የሰንደቅ ዓላማ ቀን በዓል የተዘጋጁ መልዕክቶች ከተደመጡ በኋላ የበዓሉ ፍፃሜ ሆኗል፡፡

# ለሰው ሀብት ሥራ አመራር ደጋፊ የስራ ሂደት ባለሙያዎች ስልጠና ተሠጠ

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትና ፍትህ ቢሮ ዓመታዊ ዕቅዳቸውን መሠረት በማድረግ ከሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ የሠው ሀብት ሥራ አመራር ዋና የስራ ሂደት ጋር በመተባበር ከክልል፣ ከዞን፣ ከወረዳና ልዩ ወረዳ ለተውጣጡ የሴክተሩ የሠው ሀብት ሥራ አመራር ደጋፊ የስራ ሂደት ባለሙያዎች ከ10/02/-14/02/2002

ዓ/ም ለአምስት ተከታታይ ቀናት የቆየ ስልጠና በፋራ ኮሌጅ በሰው ሀብት ሥራ አመራር ዋና የሥራ ሂደት ፈፃሚዎች ተሰጥቷል፡፡ ስልጠናውን የከፈቱት አቶ ታረቀኝ አበራ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት ባሰሙት ንግግር ስልጠናው ከስራቸው ጋር ቀጥታ ተያያዥነት ያለው በመሆኑ አቅማቸውን አጉልብተው ወደ ሥራ ገበታቸው ሲመለሱ በተሠማሩበት የሥራ መስክ በመፈፀም አቅም ረገድ የታየውን ክፍተት በማጥበብ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ሀገራችን በምታራምደው ልማትና ዴሞክራሲ ላይ ለውጥ ለማምጣት ስልጠናው አጋዥ ኃይል መሆኑን ተረድተው በንቃት እንዲሳተፉ አሳስበዋል፡፡ ስልጠናው በዋናነት የጥናት ሰነዱን በማስተዋወቅ በማሚላት፣ በዲስፕሊንና በአገልግሎት መቋረጥ አፈፃፀም መመሪያ ላይ በማተኮር ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተዘጋጀ ሲሆን 86 ወንዶችና 34 ሴቶች በድምሩ 120 የሰው ሀብት ሥራ አመራር ደጋፊ የስራ ሂደት ባለሙያዎች ተካፍለዋል፡፡



ለሰው ሃብት ስራ አመራር ደጋፊ የስራ ሂደት የተሰጠ ስልጠና

ስልጠናውን የሠጡ ወ/ሪት ምዕራፍ በላይና ወ/ሪት አብነት ቴሶ የሰው ሀብት ሥራ አመራር ዋና የሥራ ሂደት ፈፃሚዎች ሲሆኑ አሳታፊና ግልፅ በሆነ መንገድ የሠጡት ስልጠና ግንዛቤ ያስጨበጠ መሆኑን ተሳታፊዎቹ ከሠጡት አስተያየት ለመረዳት ተችሏል።

ወ/ሮ አዛለች ለማ በሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ የሠው ሀብት ሥራ አመራር ዋና የስራ ሂደት ባለቤት በስልጠናው ሂደት ከተሳታፊዎች ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ የሠጡ ሲሆን አንዳንድ የተነሱ አስተያየቶችን እንደ ግብዓት በመውሰድ በቀጣይ በምናደርገው ውይይት መመሪያዎችን በመፈተሽ ማሻሻያ የምናደርግበት ሁኔታ ይኖራል ሲሉ ገልፀዋል።



የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

በመጨረሻም ለተሳታፊዎች የተዘጋጀውን የምስክር ወረቀት ከሰጡ በኂላ የሥራ መመሪያ አስተላልፈው ስልጠናው ተጠናቋል።

## በ BSC /ሚዛናዊ ስኮርካርድ/ ዙሪያ/ ለባለሙያዎች የአሠልጣኞች ስልጠና ተሠጠ

በፌዴራል አቅም ግንባታ ሚኒስቴርና በደቡብ ክልል አቅም ግንባታ ቢሮ ትብብር ከአስር ቢሮዎች ከየስራ ሂደቱ ለተውጣጡ ባለሙያዎች ከ14/03/-18/03/02 ለአምስት ተከታታይ ቀናት በስራ አመራር ተቋም አዳራሽ በ BSC/ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ሥርዓት/ ዙሪያ የአሠልጣኞች ስልጠና በፌዴራል አቅም ግንባታ ባለሙያዎች ተሰጠ፡፡ ስልጠናው በዋናነት ዓላማ ያደረገው የውጤት ተኮር ስርዓትን ምንነትና ጥቅም ማስገንዘብ፣ የውጤት ተኮር ስርዓት በዘጠኝ ደረጃዎች እንዴት እንደሚታቀድ ለማሳወቅ እና የተቋምን የውጤት ተኮር ዕቅድ ለማዘጋጀት የሚያስችል ክህሎት ለማሳደግ በሚሉ ርዕሶች ዙሪያ ሲሆን በሀገራችን በመካሄድ ላይ ያለውን የትራንስፎርሜሽንና የተሃድሶ ጥረት ከስትራቴጂ ጋር አስተባብሮ ተያያዥነት ባለው መልክ ለመምራት ውጤት ተኮር የስርዓት ምስረታችንን በባላንነድ ስኮርካር ቅኝት መቅረፅ ጠቃሚ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ባለንስድስከር ካርድ የተቋማትን ስኬት ከፋይናንስ ውጤታማነት ባሻገር የሚያይና ለተገልጋዮች ተጨማሪ እሴትና እርካታን መፍጠር የሚያስችል እንዲሁም ተቋማዊ ራዕይን ለማሳካት የሚነደፉ ስትራቴጂዎችን አፈፃፀም ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ቁልፍ የአፈፃፀም መመዘኛዎች እየተዘጋጁ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ስለሚያደርግ ባላንስድ ስኮር ካርድ ከሌሎች የአፈፃፀም ምዘና ማዕቀፎች የተለየና ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ የአዲሱን ሥርዓት ምስረታ ለማፋጠን እንደሚረዳ አሠልጣኞቹ ገልፀዋል፡፡ ስልጠናው በገለፃ፣ በቡድን ውይይትና መልመጃዎችን በመስራት አሳታፊነት ባለው መንገድ ሲሰጥ ቆይቶ ተጠናቋል፡፡

**ራዕያችን በ2010 ዓ/ም በሁለንተናዊ መልኩ አቅሙ የጎለበተ ድህነትንና ኋላ ቀርነትን በጽናት የሚዋጋ አመረር ፣ ሲቪል ሰ`ርቫንት፣ የሲቪክ ማህበረሰብና ተቋማት ተፈጥሮ ማየት ነው ፡፡**

# የዓለም ኤድስ ቀን በደማቅ ሥነ ሥርዓት ተከበረ

???? ??? ??? ??? 22/ Dec 1/ ?? ?? ???? ???? ?? ? ? ?? ?2002 ?.? ???? ???? ??? ? ? ?? ?? ???? ??? ???? ???? ????? ??? ?? ? ?? ?? ??? ???? ??? ? ? ? - ???? ????? ??

???? ???? ?? ?? ???? ???? ???? ???-?? ?? ? ??? ? ????? ?? ? ???? ?/? ? ? ???? ??? ????? ??? ?? ??? ? ??? ???? ???? ?? ??? ????? ?? ?? ???????



የበዓሉ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት

?? ??? ??? ???? ????? ?? ?? ?? ???? ???? ??? ? ???? ?? ?? ? ??? ????? ??? ???? ?? ?? ????? ??? ? ? ????

???? ??? ?????? ?? ? ???? ?? ?? ??? ?? ???? ?? ??? ??? ??? ? ???? ???? ? ??? ???????



አቶ በላይ አበበ በዓሉን በንግግር ሲከፍቱ

???? ????? ??-???? ???? ? ??? ?? ??? ????? ????? ??? ??? ?? ? ??? ?????? ? ?? ??? ????? ???? ???? ???? ? ??? ????? ?????? ????? ???? ??? ?? ????? ???? ?? ??? ?? ?? ??? ? ?? ?? ????? ? ? ???? ????? ?????? ????? ??? ??? ???????



## የጥያቄና መልስ ውድድር

???? ???? ??? ?? ????? ?????? ? ?? ?? ????? ???? ??? ? ???? ??? ? ??? ??

??? ?? ?? ? ?? ? □□ተ□መሬ ?? ? ? ??? ? ?-? ??? ???? ???? ??? ?????

## ተስፋን የሚያመለክቱ አባባሎች

- ተስፋችንን የሚሸረሽር ፍርሀትን መሸከም የውድቀታችንን ጊዜ ይበልጥ ያፋጥነዋል !! / ጂንኤፍ ኬኔዲ/
- የአንድን ሰው ብልሀት ከምኞቱና ከተስፈው ተነስተን ማወቅ እንችላለን ። /ማዘር ትሪዛ/

# ዜና እረፍት

አቶ ከድር መሀመድ በአቅም ግንባ□ ቢሮ በ□ረ-ኤች-አይ-ቪ ሜይንስትሪሚንግ ዩኒት ኦፊሰርነት ተመድበው ሲሰሩ ቆይተው ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ጥቅምት 1 ቀን 2002 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ ለአቶ ከድር መሀመድ ቤተሰቦች መጽናናትን እንመኛለን፡፡



አቶ ከድር መሀመድ እኚህ ነበሩ!

## ከሥራ ባልደረቦቹ

## ዕጣ ፋንታህ ሆነ!

□□ሪ ተቀብለህ
አዲስ ቤትም ሰርተህ
አዲስ ቢሮ ገብተህ
ለሥራ አስፈላጊ ቁሳቁስ ተረክበህ
ሥራ ባል□ረባ ጃ□ኛም ተ□□ቀህ
ሁሉን አስተከክለህ
በአዲሱ አሰራር በትጋት ልትሰራ
ለሁሉም ቃል □ብተህ
ጠዋት ስንጠብቅህ መደበኛ ቦ□ህ
ለከስ አምርረሃል ቀረህ እንደወጣህ፡፡
ሰው መሆንህ ከንቱ
ስትመስለን ብርቱ
ከምኔው ተረ□ህ
ቀልዱም ቁም ነገሩም ሁሉም
በአንዴአቃተህ፡፡
ቀሳ□□ በሽታ ከገር እንዲጠፋ
□□ታ እኩልነት ባገር እንዲስፋፋ
ደፋ ቀና ስትል ልትታደግ ወገን
ወንድማችን ከድር ብዙ ለፍተህ በቅን
ምንም ሳትናገር ምንም ሳ□□ራ
ለማን ብለህ እንደሄድክ ልጆችህን አደራ
ድንገት ሳታስበው በላይህ ዳመነ
ከዚህ ዓለም መለየት ዕጣ ፋንታህ ሆነ፡፡

ሠ.አ

# መረጃ ቢያስፈልግዎ

| አቅም ግንባ□ ቢሮ | | | |
|---|---|---|---|
| | ስልክ | ፋክስ | ፖስታ |
| ቢሮ □ላ□ | 04-62-20-61-43 | 04-62-20-61-44 | 1157 |
| □ሊኮተ ዋና የስራ ሂደት | 04-62-20-65-72 | 04-62-20-93-86 | |
| የለውጥ ፕሮግራሞችና ጥናትና ትግበራ ዋ/የሥራ ሂደት | 04-62-20-67-52 | 04-62-20-86-73 | |
| የል/ዕ/ዝ/ክትትል ደጋፊ የስራ ሂደት | 04-62-20-45-25 | | |
| የሰው ሃብት ስራ አመራር ደጋፊ የሥራ ሂደት | 04-62-20-61-45 | | |
| □መንግስት ኮሚኒኬሽን የስራ ሂድት | 04-62-20-44-98 | | |
| □□□ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር | 04-62-20-84-98 | | |
| □□ፈ-ኤችኤ ቪ እና ስርዓተ ጾታ | 04-62-20-33-89 | | |
| **ሥራ አመራር ተቋም** | | | |
| □□ሬ□ተር ቢሮ | 04-62-20-20-09 | 04-62-20-53-69 | 215 |
| የስራ አመራርና የመሪነት ልማት ዋና የሥራ ሂደት | 04-62-21-10-61 | 04-62-20-46-34 | |
| የል/ዕ/ዝ/ክትትል ደጋፊ የስራ ሂደት | 04-62-20-18-82 | | |
| □□□/ፋ/ን/አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት | 04-62-20-14-63 | | |
| የሰው ሃብት ስራ አመራር | 04-62-20-20-08 | | |
| ኦዲት አገልግሎት | 04-62-20-20-06 | | |
| **ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ** | | | |
| ሥራ አስኪያጅ | 04-62-20-10-64 | 04-62-20-47-61 | 311 |
| የሰው ሃብት ስራ አመራር ዋና የስራ ሂደት | 04-62-20-16-39 | | |
| □ቅሬታ ማስተናገኛ ሥርዓት ዋና የስራ ሂደት | 04-62-20-12-93 | | |
| የመረጃ አያያዝና የሪከርድ ዋና የስራ ሂደት | 04-62-20-10-63 | | |
| የክልሉ ቴክኒካል አማካሪ ቲም | 04-62-20-45-35 | | |

**አቅም ግንባ□ ቢሮ-** Website – www.snnprcapacity.gov.et

**ሥራ አመራር** Website –snnprmi-gove.et